# ይቅርታ! ከዜሮ በታች ከሆኑ ሰዎች ጋር አብረን አንደመርም !!

( አሥራደው ከፈረንሳይ )




ከአንድ መቶ ቀናት በፊት አዲስ የተሰየሙት የኢትዮጵያ ጠ/ ምኒስትር ዓብይ አህመድ፤ ወያኔ ለ27 ዓመታት ያህል እየኮተኮተ ውሃ በማጠጣት ያሳደገው፤ እሾሃማ የጎሳና የዘር ፖለቲካ፤ በያዘው መንገድ መቀጠል እንደማይችል፤ የህዝቡን ቁጣ ይበልጡኑ የወጣቱን ክፍል ቆርጦ መነሳት በማየት፤ ከአሁን በኋላ በተለመደው ጎሰኛና ሌሎችን አግላይ በሆነ ዘረኛ ፖለቲካ መቀጠል እንደማይቻልና፤ ሕዝብ ለሚጠይቀው መልስ ካላገኘ፤ ሁሉኑንም የወያኔ አባላት ከነ አጫፋሪዎቻቸው፤ ዓብይንም ጨምሮ ጠራርጎ እንደሚወስዳቸው ቀድመው ከተረዱ የውስጥ ፖለቲከኞች መሃል፤ ለማ መገርሳና፤ ጠ/ ምኒስትር ዓብይ አህመድ ናቸው ።

ጠ/ ምኒስትር ዓብይ አህመድና ለማ መገርሳ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፤ ለወያኔዎችም ጭምር ባለውለታ ናቸው ። አለመታደል ሆኖ በወያኔዎች በኩል እጃቸው እንደ አመድ አፋሽ ተቆጠረ እንጂ ። አሁንም በብብታቸው ውስጥ ያሉት የቀበሮ ባህታዊዎች፤ ፈጥነው ኮታቸውን በመገልበጥ፤ አብረዋቸው ያሉ መስለው እንዳያጠፏቸው ቢጠነቀቁ ይበጃል ። የተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ እንዳይነጠቅ፤ የተዘረፈው የአገራችን ሃብት ከአገር እንዳይወጣ፤ ሁላችንም ለአገራችን ዘብ መቆም ይኖርብናል* ።

- ጠ/ ምኒስትር ዓብይ አህመድና ለማ መገርሳ፤ የሕዝቡን ትኩሳት፤ ልክ እንደ ሙቀት መለኪያ፤ በመለካትና ፤ የሕዝቡን በተለይም የወጣቱን የልብ ትርታ በተገቢው ደቂቃና ሰዓት በማዳመጥ፤ "ኢትዮጵያዊነት ሱስ ነው" በሚልና "በፍቅር አብረን እንደመር" በማለት መልስ ባይሰጡ ኖሮ፤ ሕዝባዊው ማዕበል ወያኔን እራሱ በቆፈረው የጎሰኝነትና የዘረኝነት ጉድጓድ ቀብሮ፤ ከመሃላቸው ለወሬ ነጋሪ እንኳን የሚተርፍ አይኖርም ነበር ።

- ጠ/ ሚንስትር ዓብይ አህመድና ለማ መገርሳ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብም በጅተዋል፤ ለ27 ዓመታት ከወያኔ ጋር ሆነን፤ በጎሳ፤ በዘርና በጥላቻ ከፋፍለን ያቃቃርነውን ሕዝብ፤ በይቅርታና፤ በፍቅር በማስተሳሰር የተመኘውን አብሮነት፤ በመቀበል፤ በአንድነቱ እንካሰው በማለታቸው አከበራቸው ወደዳቸውም ።

- ለ27 ዓመታት የኢትዮጵያን ጡት እየነከሱ፤ የኢትዮጵያን ስም ለመጥራት ቆዳቸውን ያሳክካቸው የነበሩ፤ ጓደኞቻቸው ጥርሳቸውን ቢነክሱባቸውም፤ ሳይፈሩ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከነሰንደቅ ዓላማዋ አከበሩ፤ ሕዝብም በምላሹ አከበራቸው ፍቅሩንም ቸራቸው ።

- ልዩነት ውበት፤ ልዩነት ጥበብ፤ ልዩነት ፈጠራ፤ ልዩነት የእድገት ፈር ቀዳጅ ጮራ መሆኑን የማያምኑ ቢኖሩ፤ ጭንቅላታቸውብ በሸንፍላቸው ውስጥ ቀብረው፤ የሚያንኳርፉ ሆዳሞች ብቻ ናቸው ።

- ፍቅር፤ ወንድማማችነት፤ አብሮነትና ፤ ጀግንነት፤ ከአያት ቅድም አያቶቻችን፤ የወረስነው ኢትዮጵያዊ ባህላችን እንደመሆኑ ሁሉ :

ሌቦችን፤ ነብሰገዳዮችን፤ ውሸታሞችንና አገር ከሃዲዎችን በእጅጉ የምንጠየፍ ኩሩ ኢትዮጵያውያን ነን ::

**ግን ?! ግን ?!**

- ክቡር ጠቅላይ ምኒስትር: እስቲ ልጠይቆት፤ በፍቅር እንደመር ሲሉ፤ ከነማን ጋር ነው የምንደመረው ?

* የእናት አገራችን ኢትዮጵያን ስም ለመጥራት ይጠየፉ ከነበሩ፤ አጠያፊዎች ጋር ?!

የቀረው ይቅር እንጂ፤ ከነዚህ አጠያፊዎች ጋር እኔና መሰሎቼ አብረን አንደመርም ::

* የአገራችንን ሃብት ለ27 ዓመታት ከዘረፉ ሌቦች ጋር?

በጭራሽ ! ሕዝባችንን በሌብነት ካደኸዩ ሌቦች ጋር እኔና መሰሎቼ አብረን አንደመርም ::

* በወጣት ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ደም፤ እጃቸውን ከታጠቡ ነብሰ ገዳዮች ጋር ?

በፍጹም ! ክቡር የሆነ የሰውን ልጅ ህይወት፤ በወጣትነቱ ከቀጠፉ ነብሰ ገዳዮች ጋር እኔና መሰሎቼ አብረን አንደመርም ::

* ይጦረኛል ትጦረኛለች ብለው፤ ቆሎና እንጀራ እየሸጡ ልጆቻቸውን ያስተምሩ የነበሩ ደካማ እናቶችና አባቶች ልጆችን በጠራራ ፀሐይ ከረሸኑ ነብሰ ገዳዮች ጋር ?!

በጭራሽ ! የነዚህ ወገኖቻችንን ዕንባ የሚያብስ **ፍትህ** ሳይኖር እኔና መሰሎቼ ከነብሰ ገዳዮች ጋር አብረን አንደመርም ::

* የበሉትን ከትፎ እያገሱ፤ የጠጡትን ውስኪ፤ በተራቡ በወገኖቻችን ላይ ያቀረሹ ከነበሩ፤ ቅርሻታሞች (ሆድ አምላኩዎች) ጋር፤ እኔና መሰሎቼ አብረን አንደመርም ::

* ማንነታችንን ብቻ ሳይሆን፤ ምኞታችንና ሕልማችንን ከሰረቁ ሌቦች ጋር፤ እኔና መሰሎቼ አብረን አንደመርም ::

በሳይንሳዊ ቀመር፤ ከዜሮ በታች ከሆኑ ሰዎች ጋር አብሮ መደመር፤ ትርፍ ኪሳራ ነው ::

<u>ለምሳሌ፤</u> 4 ንጹህ ሰዎች ፤ ከዜሮ በታች ከሆኑ -5 ሌቦች ጋር ሲደመሩ፤ ውጤቱ ከዜሮበታች -1 ይሆናል ::

<u>ልጨምር፤</u> 3 ንፁህ የሆኑ ሰዎች፤ ከዜሮ በታች ከሆኑ -6 ሰዎች ጋር ሲደመሩ፤ ውጤቱ ከዜሮ በታች የሆኑ -3 ይሆናሉ ::

ከዜሮ በታች የሆኑ - 10 ሰዎች፤ ከዜሮ በታች ከሆኑ -5 ጋር ሲደመሩ፤ ውጤቱ ከዜሮ በታች የሆኑ -15 ሰዎች ይሆናሉ ::

ክቡር ጠቅላይ ምኒስትር! ታዲያ እርሶስ ምን ሊያተርፉ? እኛስ ምን ሊተርፈን ነው? ከዜሮ በታች ከሆኑ ሰዎች ጋር አብራችሁ ተደመሩ የሚሉን ?!!

* ገና በእናቱ ማህጸን ያለ ጽንስ እንኳ ሳይቀር፤ እዳ ከፋይ ካደረጉ ሌቦች ጋር እንዴት አብረን እንደመራለን ?!

* ባንድ ወቅት: እርስዎም " ጅቦች" ሲሉ ጠርተዋቸዋል፤ ታዲያ እንዴት ከጅቦች ጋር አብረን እንደመራለን ?

* የዛሬ አዘራራፊና ዘራፊ ሌቦችን፤ ነብሰገዳዮችን፤ ድሃ እያፈናቀሉ መሬት ቸብቻቢዎችን፤ ከሃዲ አገር ሻጮችን ፤ የሚዳኝ **ፍትህ** ሳይኖር፤ የነገ ሌቦችና ነብሰገዳዮች፤ በየትናው ሕግ ሊዳኙ ነው ?

- ይቅርታ! እኛ ኢትዮጵያዊያን ኩሩ ዜጎች በመሆናችን፤ ከዜሮ በታች ከዘቀጡ ሰዎች ጋር አብረን በመደመር፤ እንደነሱ አንዘቅጥም !!

በቅድሚያ ፍትህ ለተነፈጉ ወገኖቻችን **ፍትህ !!**

ለ27 ዓመታት በተለያዩ ጽሑፎቼ በተጠቀምኩበት የጽናት መፈክር ላብቃ፤

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ !!

እግዚአብሔር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይባርክ !!